# የመኖሪያ ቤት መዋለ ሕጻናት ማቅረብ

## በመኖሪያ ቤትዎ የቤተሰብ መዋለ ሕጻናት የሥራ ፈቃድ ማግኘት

በዋሽንግተን ስቴት ውስጥ ማንኛውም በራሱ/ሷ መኖሪያ ቤት ውስጥ በመደበኛነት ለልጆች የመዋለ ሕጻናት አገልግሎት ለማቅረብ የሚከፈለው ግለሰብ የሥራ ፈቃድ ማውጣት ያስፈልገዋል (ልጆቹ ከዚያ ግለሰብ ጋር ዝምድና ካላቸው በስተቀር)። ይህም ማለት የቤተሰብ መዋለ ሕጻናት አገልግሎት አቅራቢዎቹ ከቅርብ ዘመዳቸው ውጭ ለሆኑ ሕጻናት የመዋለ ሕጻናት አገልግሎት ለመስጠት የሥራ ፈቃድ ያስፈልጋቸዋል ማለት ነው። በቤትዎ ስፋት፣ በትምህርትዎ ደረጃና ስልጠና ረዳት በመኖሩና ባለመመኖሩ ሁኔተ መሠረት እስከ ለ 12 ልጆች አገልግሎት ለማቅረብ የሥራ ፈቃድ ሊያገኙ ይችላሉ። የሚኖሩት የመዋለ ሕጻናቱ ባለበት መሆን አለበት።

**የሥራ ፈቃዱ ጥቅም**

- ባለ የሥራ ፈቃድ መሆን አስቸጋሪ አይደለም እናም ለሚያውሉት ጊዜ ተጠቃሚ የሚሆኑበት ነው። በሕግ ከማስፈለጉም በተጨማሪ የሥራ ፈቃድ ያለው የመዋለ ሕጻናት አገልግሎት አቅራቢ መሆን ከመዋለ ሕጻናት አገልግሎት ምንጭ መምሪያ በነፃ የመዋለ ሕጻናት ዝርዝር ላይ እንዲመዘገቡ ይሆናሉ። በዝርዝሩ ላይ ለመውጣት (206) 329-5544 ይደውሉ።

- የአንዳንድ የምግብ ወጪዎችዎን ለሚተካልዎት ከፌደራል የምግብ ፕሮግራም ጋር ተካፋይ መሆን ይችላሉ።

- ግብር በመከፈል ላይ ጥቅም ሊያገኙ ይችላሉ። የሥራ መረጃን በመዝገብ ስለመያዝ አስፈላጊ ነጥቦች ለማወቅ ለአይአርኤስ በ 1-800-829-1040 ይደውሉ። ስለ ግብር እና የሥራ መረጃን በመዝገብ ስለማስቀመጥ የሚረዱ መጽሐፎች ለሬድሊፍ ፕረስ በ 1-800-423-8309 በመደወል ይገኖሉ።

- ካልታሰበ ዕዳ መጠባበቂያ መድን ሊገዙ ይችላሉ።

- ከስቴቱንና ከስቴቱ የሥራ ፈቃድ ሰጪ መረጃዎችን ማግኘት ይችላሉ።

- ከብዙ የማህበረተሰብ አገልግሎቶች የሚቀርቡ የሥራ መርጃዎችን ሊጠቀሙ ይችላሉ።

- ስለ ሥራዎ በአካባቢ ጋዜጣዎች ላይ ሊያስተዋውቁ ይችላሉ።

- ለካስኮ አባልነት ብቁ ይሆናሉ።

በመኖሪያ ቤትዎ ውስጥ የመዋለ ሕጻናት ፕሮግራም ለመጀመር ፍላጎት ካለዎት የመጀመሪያው እርምጃ በልጅ ማሳደጊያና ቅድመ ትምህርት ክፍል (ዲቪዥን ኦፍ ቻይልድ ኬር ኤንድ ኧርሊ ለርኒግ) የሚሰጠውን የሥራ ፈቃድ ገለጻን መከታተል ነው። በገለጻው ላይ የሥራ ፈቃዱን ስለሚመለከተው ሕግ ይማሩና ስለ ሥራ ፈቃድ አወጣጥ፣ የስቴቱ ደንቦችና ተጨማሪ መረጃዎች ያለበት የማመልከቻ ቅጽ ከመመሪያው ጋር ያገኖሉ። ለአንዳንድ የተወሰኑ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የሥራ ፈቃድ ሰጪው ይገኖሉ። ኪንግ ካውንቲ በ2 የሥራ ፈቃድ ማውጫ አካባቢዎች የተከፈለ ነው፣ እርስዎ በሥራ ፈቃድ ማውጫ አካባቢዎ ሳይወሰኑ ባንዱ ላይ በገለጻው ላይ ሊካፈሉ ይችላሉ።

ስለ የሥራ ፈቃድ አስፈላጊ ነጥቦች እዚህ ላይ ጠቅ ጠቅ ያድርጉ - (ለሁሉም አካባቢዎች)

- **ዲቪዥን ኦፍ ቻይልድ ኬር ኤንድ ኧርሊ ለርኒግ - ሪጅን 4A (ሲያትል) ማሳሰቢያ፣ የሪጅን 4A ዌብ ሳይት በአሁኑ ወቅት በሥራ ላይ አልዋለም - ለተጨማሪ መረጃ እባክዎን 206 721-6941 ይደውሉ።**
- የሥራ ፈቃድ ሰጪዎን ይፈልጉ
- የገለጻው መሠረታዊ ሀሳቦች
- የገለጻው የጊዜ ምድብ

- **ዲቪዥን ኦፍ ቻይልድ ኬር ኤንድ ኧርሊ ለርኒግ - ሪጅን 4B (ኬንት)**
- የሥራ ፈቃድ ማውጫ የሥራ ባልደረቦች
- ገለጻና የአገልግሎት አቅራቢ መሠረታዊ መረጃዎች

**የመዋለ ሕጻናት ምንጭ የሥራ ፈቃድ እንዲያወጡ የሚረዱዎት የሥራ ባልደረቦች አሉት።**
- የሥራ ፈቃድ ረዳት ሠራተኛ